

# <u>ልብ በል አገሬው !</u>

ዘመን ተሻጋሪ ፣ ታሪክ እንድንሰራ፣

ተነስ የአገሬ ልጅ ፣ እናብር በጋራ፣

በሥራ ጠንክረን ፣ አስበን ከሰራን፣

ዘር መቁጠሩን ትተን ፣ ኢትዮጵያን ካስቀደምን፣

ወደጥንቱ ክብር፣ ወደከፍታችን፣

ወደ ሥልጣኔ፣ እንገሰግሳለን ፣

ማንም አያቆመን ፣ ማንም አይጎትተን።

ተሰናክለን ቆመን ፣ ልክ እንደባቡሩ፣

ሥልጣኔን ትተን ፣ ወርደን ከዘቀጥን፣

የአባቶቻችን ገድል እኛ ካንጓጠጥን፣

በቀደዱልን ቦይ፣አብረን ከፈሰስን ፣

ለጣሊያን አሽከሮች ፣ መንገድ ከከፈትን፣

ልክ እንደ አባይ ወንዙ ፣ ግብጽ እናለማለን ፣

ሌላውን አስርበን ውሃ ፣ እንገብራለን ፣

ላገሬው ጨለማ ፣ ለጎረቤት ብርሃን፣

በመፅዋት እየኖርን ፣ እኛ እንራባለን፣

ከሌሎች ሃገሮች ፣ እርዳታ እንወስዳለን።

በቀደዱልህ ቦይ ጨርሶ አትፍሰስ፣ ከዘር መስተዳደር ገድብ ራስህን ፣

ዓባይንም ገድብ ፣ አትውረድ ቁልቁሉን፣

ከኛ ላይ ጠራርጎ፣ የወሰደውን ሃብት፣

ሕዝቦቹን አስርቦ ፣ እርከን ሳይሰሩለት ፣

ስንቶቹ አለፉ ፣ በሱ በመቆጨት ።

ማመዛዘን ትተን ፣ ወደታች ከወረድን፣

መከራ መዓቱን ፣ በኛ ላይ አብዝተን፣

ሠላም አናመጣም ፣ ሃገር  እንጎዳለን።

በሚኮራ እንኩራ ፣ ገድለ አባቶቻችን ፣

ልበ ብሩህ  እንሁን ፣ እንተው ቁልቁለቱን።

**መይሳው ከምድረ ስዊድን**

29 december 2019